የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር

የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት

የሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ

514/2013

ሐምሌ /2008

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት

የሽያጭ አፈጻጸም መመሪያ

514/2013

ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ የልማት ድርጅቶች እና አክሲዮን ማህበራት በተለያዩ የፕራይቬታይዜሽን ስልቶች በዋናነት በሽያጭ ወደ ግል ባለሀብቶች በማዛወር ውጤታማ ሥራ እያከናወነ እንደሆነ ይታወቃል።

ካለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚሄድ ወጥ የሆነ የመንግሥትን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል በግልጽነትና በተጠያቅነት መንፈስ የሽያጩን ሂደት ለማስኬድ የሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚንስቴር በጨረታ ሽያጭ አወዳድሮ ወደ ግል ይዞታ ለሚያዛውራቸው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች/አክሲዮን ማህበራት የሚቀርቡትን ጨረታዎችና የመወዳደሪያ ሃሣቦች/ፕሮፖዛሎች/ መርምሮ የውሣኔ ሃሣብ የሚያቀርብ አንድ የሽያጭ ውድድር ገምጋሚ ኮሚቴ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ኮሚቴው ተግባሩን እና ኃላፊነቱን በግልጽነት፤ በፍትሓዊነት እና በተጠያቂነት መንፈስ ለማካሄድ የሚያስችል አሰራር በመመሪያ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916 /2008 አንቀጽ 31 (ለ)(9) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia ...istry of Public Enterprises

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 514/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "የልማት ድርጅቶች" ማለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ናቸው።
2. "ሽያጭ" ማለት አንድን አክሲዮን ማህበር ወይም ድርጅት ወይም የድርጅት ቅርንጫፍን በጨረታ ወይም በሌላ የሽያጭ ስልት ከሚገዛ ሰው ወይም ድርጅት ገንዘብ የመቀበል፤ውል የመፈፀምና የተሸጠ አክሲዮን ማህበር ወይም ድርጅት ወይም የድርጅት ቅርንጫፍን የማስረከብ ሂደት ነው።
3. "ጨረታ" ማለት የጨረታ ማስታወቂያ ይፋ ከሆነበት ወይም የጨረታ ጥሪ/ ግብዣ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ አሸናፊው ተለይቶ ውል እስኪፈረም ድረስ ያለውን የሽያጭ አፈፃፀም ሂደት የሚገልጽ ነው።"
4. "የጨረታ ሠነድ" ማለት አንድን የልማት ድርጅት/አክሲዮን ማህበር በሽያጭ ወደ ግል ይዞታና አስተዳደር ለማዛወር እንዲቻል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንደ አስፈላጊነቱ የሚያዘጋጀው የሽያጭ ሂደቱንና አስፈላጊ መስፈርቶችን በዝርዝር በመያዝ ተዘጋጅቶ ለተወዳዳሪዎች የሚሸጥ ሠነድ ነው፤
5. "ተጫራች/ተወዳዳሪ" ማለት አንድን የልማት ድርጅት/አክሲዮን ማህበር ለመግዛት የጨረታ ሰነድ ገዝቶ ለመወዳደር የመጫረቻ ሀሳብ ያቀረበ ግለሰብ/ ቡድን ወይም ተቋም ማለት ነው።
6. "የተራዘመ ክፍያ" ማለት ገገርዎች በፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም ለሚሸጡ የልማት ድርጅቶች ፤ ቅርንጫፎች ና አክሲዮን ማህበራት በውለታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት ቅድሚያ ክፍያውን ከፈፀሙ በኋላ በተራዘመ የክፍያ አሰራር ተጠቃሚ የሚሆኑት የውጭ አገር ባለሀብቶች ቢበዛ እስከ 3 ዓመታት ፤ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች እስከ 5 የሚያጠናቅቁት ቀ[illegible] ነው።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia ... Public Enterprises

7. "ሚኒስቴር ማለት" የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ነው፡፡

3. <u>የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በሁሉም ለሚ/ር መ/ቤቱ ተጠሪ በሆኑ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች/አክሲዮን ማህበራት እና ቅርንጫፎቻቸው ሽያጭ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4. <u>መርሆዎች</u>

ማናቸውም የመንግሥት ልማት ድርጅቶች/አክሲዮን ማህበራት ሽያጭ ለማስፈፀም የተሰጠ ሥልጣን እና የሽያጭ አፈፃፀም ተግባር የሚከተሉትን መርሆዎችን መከተል ይኖርበታል፡፡

1. በሽያጭ አፈፃፀም ረገድ ሽያጩ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘቱን፣ ይህም ማለት የአፈፃፀም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ፣
2. በሌሎች ህጎች ወይም በዚህ መመሪያ በግልጽ ካልተቀመጠ በቀር ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በዜግነት ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያዘ ሌሎች ምክንያቶች በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ እንዳይሳተፉ አለመከልከል ወይም አድልዖ አለማድረግ፣
3. ከመንግሥት ልማት ድርጅቶች/አክሲዮኖች እና ቅርንጫፎቻቸው ሽያጭ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የሚሰጡ ውሣኔዎች እና የሚወሰዱ እርምጃዎች ሀላፊነትንና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ መፈጸም ፣
4. ማናቸውም የመንግሥት ልማት ድርጅቶች/አክሲዮኖች የሽያጭ ውሣኔ የሚሰጥበት መስፈርት እና በእያንዳንዱ ሽያጭ ላይ የሚሰጠውን ውሣኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልፅ ማድረግ፣
5. በመንግሥት ኢንቨስትመንት አዋጅ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት መሠረት የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብቶች የሚስተናገዱበትን መርሆዎች መከተል አስፈላጊ ነው፡፡

ክፍል 2

የሸያጭ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

5. የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ ተግባርና ኃላፊነት

ሽያጩን በማስፈጸም ረገድ የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

5.1 የልማት ድርጅቶችን እና የአክሲዮን ማህበራትን የሽያጭ ዕቅድ ያዘጋጃል፣

5.2 የሽያጭ ጨረታ ሰነድ ተሟልቶ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፤

5.3 የጨረታ ሰነድ ይሸጣል፣ በጨረታ ሰነዱ ላይ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ማብራሪያ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፣

5.4 የጨረታ ሰነዶች በሥራ ክፍሉ ተገምግመው እንዲጸድቁ ያደርጋል

5.5 ለጨረታ አሸናፊዎችና ተሸናፊዎች የጨረታው ውጤት እንዲገለጽላቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ይከታተላል

5.6 በጨረታ አሸናፊዎችና በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሽያጭ ውል እንዲፈረም ያደርጋል፣

5.7 የጨረታ አሸናፊዎች በውል ስምምነታቸው መሠረት መፈጸማቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡

5.8 የሽያጭ ሰነዶችን አደራጅቶ ይይዛል ፣ይጠብቃል፣ ሲጠየቅ ለሕጋዊ አካላት ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

5.9 የጨረታ ሰነዶቹ በሙሉ ሥርዓት በያዘ መልኩ በኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ እና በሪከርድና ዶክሜንቴሽን ክፍል ተደራጅተው እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡

5.10 በሚኒስቴር መ/ቤቱ የልማት ድርጅቶችን /አክሲዮን ማህበራት በሚመለከት የተከናወኑ ሽያጮችን የሚገልጽ አፈፃፀም ሪፖርት ለሚ/ር መ/ቤቱ ያቀርባል፣

6. የሽያጭ እና ውድድር ገምጋሚ ኮሚቴ መቋቋም

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የሽያጭ ውድድር ገምጋሚ ኮሚቴ /ከዚህ በኋላ ኮሚቴው/ በመባል የሚጠራ/ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል

7. አባላት

7.1 ኮሚቴው በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚንስቴር ሚንስትር የሚመደቡ አምስት አባላት ይኖሩታል።

7.2 የኮሚቴው ሰብሣቢ እና ፀሐፊ በሚንስትር የሚሰየሙ ሲሆን የኮሚቴው ፀሐፊ ከኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ የሚቀርብ ይሆናል።

8. የኮሚቴው ተጠሪነት

ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለሚኒስትር ይሆናል።

9. የኮሚቴው አባላት አመራረጥና መመዘኛ

9.1 የኮሚቴው አባላት ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የሚመረጡ ይሆናሉ።

9.2 የኮሚቴው አባላት ቢያንስ የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው።

- ➢ በትምህርት ደረጃ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ እና ከዚያ በላይ ያለው/ያላት፤
- ➢ ማንባር ቅደም፣ብቁ፤ እና ተወዳዳሪ የሆነ/የሆነች፤
- ➢ ከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት የሚሰማው/የሚሰማት፤
- ➢ ስሙ ስና ጾዱ የሆነ እና መልካም ሥነ-ምግባር ያለው/ያላት፤
- ➢ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን /አክሲዮን ማህበራትን ለመሸጥ በተደረገው የዋጋ ትመና ዉስጥ ያልተሳተፈ/ያልተሳተፈች፤
- ➢ ከሁለት አመት ወዲህ በዲስፕሊን በመከሰስ ያልተቀጣ/ያልተቀጣች

10. የሽያጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

10.1 ተጫራቾች የመወዳደሪያ መስፈርቶችን ያሟሉ መሆኑን ያረጋግጣል

10.2 የመወዳደሪያ ሰነድ በወጣው የጨረታ ሰነድ መሠረት መሆኑን፣ መመሪያውንና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የመንግስት ሕጎችን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል።

10.3 ኮሚቴው የቀረበውን ጨረታ ዋና ይዘት የማይለውጥ ማብራሪያ ካስፈለገው ከተጫራቾች በጽሑፍ ጠይቆ ማግኘት ይችላል። የተሰጠው ማብራሪያ በሪፖርቱ ውስጥ በግልጽ መጠቀስ አለበት። ማብራሪያውም ከጠቅላላው የጨረታው ሰነዶች ጋር ተያይዞ የሚቀመጥ ነው።

10.4 ኮሚቴው ምክርና የባለሙያ እገዛ በሚፈልግበት ጊዜ ከኮርፖሬትና ፋይናንስ አስተዳደር ዘርፍ ጋር በመሆን ይሰራል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Public Enterprises

10.5 በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት የተወዳዳሪዎችን የመወዳደሪያ ሀሳቦች መርምሮ ለሚኒስትሩ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤

11. <u>የኮሚቴው ሰብሳቢ ኃላፊነት ተግባር</u>

11.1 የኮሚቴው ሰብሳቢ፣የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣

11.2 የኮሚቴውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፣

11.3 የኮሚቴው የስብሰባ ጊዜ ሰሌዳ እንዲዘጋጅ በማድረግ ስብሰባዎችን በጊዜው ይጠራል፣ ስብሰባዎቹ መደረጋቸውንም ያረጋግጣል፣

11.4 ጨረታ በሚዘጋበት ጊዜና ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ በመገኘት በዚህ መመሪያ መሠረት እንዲፈጸም ያደርጋል፣

11.5 በዚህ መመሪያ መሰረት ስራው እንዲሰራ ያደርጋል፤

11.6 ለኮሚቴው የተሰጡ ተግባር እና ኃላፊነት ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

11.7 የኮሚቴውን ውሳኔ ሪፖርት ያደርጋል፤

12. <u>የኮሚቴው ፀሐፊ ኃላፊነትና ተግባር</u>

የኮሚቴው ፀሐፊ፣ የኮሚቴ አባል ሲሆን በፀሐፊነቱ ቀጥሎ የተመለከቱትን ተግባራት ያከናውናል።

12.1 ተወዳዳሪ ለመጋበዝ የተደረጉ ጥሪዎችን /የጨረታ ሰነድ/ የሚገዙትን ሰዎች ዝርዝር መዝግቦ ይይዛል፣ በጨረታ መክፈቻው እለትም ለማመሳከሪያ ያቀርባል፣

12.2 ማናቸውንም የጨረታ ሰነዶች ሥራው ተጠናቅቆ ወደ ሚመለከተው ዘርፍ እስኪመለስ ድረስ በዚህ መመሪያ መሠረት አሟልቶ ይይዛል፣

12.3 የስብሰባ አጀንዳ ያሰራጫል፤

12.4 የኮሚቴውን ስብሰባዎችና ግምገማ ቃለጉባዔዎች አዘጋጅቶ በማስፈረም ይይዛል፣

12.5 ሪፖርቶችን ያዘጋጃል ይይዛል፣

12.6 ለሌላ ወገን መድረስ ያለባቸውን ቃለጉባዔዎችና ሪፖርቶች በበቂ ቅጅ አዘጋጅቶ ካስፈረመ በኋላ በቶሎ ለሚመለከታቸው እንዲደርስ ያደርጋል፣

12.7 ጨረታ በሚዘጋበት ጊዜና ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ በመገኘት በመመሪያው የተጣለበትን ተግባር ያከናውናል፣

12.8 የጨረታ ማስከበሪያ ይቀበላል፣ በጨረታ ሰነዱ በተገለጸው ሁኔታ መሠረት የጨረታ ማስከበሪያውን በለቱ ለፋይናንስ በጽሑፍ በማስፈረም ያስረክባል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Public Enterprises

13. የሽያጭ እና ውድድር ገምጋሚ ኮሚቴ አባላት ሥነ-ምግባር

13.1 የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሽያጭ ገምጋሚ ኮሚቴ አባል የሚሰጠው ውሳኔ በማንኛውም መልኩ ራሱን ወይም ቤተሰቡን ሲጠቅም የሚችል መሆኑን ሲረዳ ከሥራው ጋር የተገናኘ የጥቅም ግጭት መኖሩን በጽሑፍ በማሳወቅ ራሱን ማግለል ይኖርበታል።

13.2 የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሽያጭ ገምጋሚ ኮሚቴ አባል ሥራቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ወይም ሊያሳድር የሚችል ምንም ዓይነት ስጦታ ከማንም ሰው መቀበል የለባቸውም፣ በአንፃሩ የሚከተሉትን ያካተተ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

13.3 ማናቸውም የኮሚቴው አባል በማናቸውም ምክንያት ስለ ውድድሩና ስለተደረገው ግምገማ ማናቸውንም ዓይነት መረጃ በሚኒስትሩ ካልተፈቀደለት በስተቀር ተጫራቾቹን ጨምሮ ለማናቸውም ሰው ማሳወቅ ክልክል ነው።

13.4 ማንኛውም ኮሚቴ አባል ከተወዳዳሪዎች ጋር የጋብቻ፣ የደም ወይም ሌላ ማናቸውም ግንኙነት ሲኖረው ወይም ሌላ በማናቸውም ምክንያት ትክክለኛና ፍትሐዊ ስራ ለመስራት የማያስችለው ሁኔታ ሲከሰት ይህንኑ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒስትር እና ለኮሚቴው ሰብሳቢ በቅድሚያ በጽሁፍ ወዲያውኑ በማሳወቅ ራሱን ከኮሚቴ አባልነት ማግለል አለበት።ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒስትር ተተኪ ይመድባል፤

13.5 አንቀጽ 13.4 እንደተጠበቀ ሆኖ ከሌላ ወገን መረጃ ከቀረበ የኮሚቴው አባል እንዲነሳ ወይም አቤቱታ በቀረበበት ድርድር ላይ እንዳይሳተፍ ይደረጋል፤

13.6 ማንኛውም የኮሚቴ አባል በአንቀጽ 13.4 በተዘረዘሩት ምክንያት ትክክለኛና ፍትሐዊ ስራ ለመስራት የማያስችለው ሁኔታ መኖሩን እያወቀ ራሱን ከኮሚቴ አባልነት ካላገለለ አስፈላጊው የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰደወበታል።

14. የሰብሣቢው ወይም የፀሐፊው አለመገኘት

ሀ. ሰብሣቢው በስብሰባ ለመገኘት ባልቻለ ጊዜ ይህንኑ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒስትር በማሳወቅ ተተኪ ሰብሣቢ እንዲመደብ ያስደርጋል።

ለ. ፀሐፊው በስብሰባ ለመገኘት ባልቻለ ጊዜ ኮሚቴው ተተኪ ፀሐፊ መድቦ ሥራውን ይቀጥላል። ይህንንም ለሚኒስትር ያሳውቃል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Public Enterprises

14 ምልዓተ-ጉባዔና ውሣኔ

14.1 ኮሚቴው የግምገማ ሥራውን ለማከናወን ምልዓተ-ጉባዔ የሚኖረው ከአባላቱ ሁለት ሦስተኛው ሲገኙ ነው።

14.2 የኮሚቴው ውሣኔ የሚባለው ከተገኙት ሁለት ሦስተኛ አባላት የድምጽ ብልጫ ያገኘው ሃሣብ ነው። ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሣቢው ያለበት ወገን ድምጽ የኮሚቴው ውሣኔ ሆኖ ይቆጠራል።

ክፍል 3

ስለ ሽያጭ ዕቅድ

15 የሽያጭ ዕቅድ ስለማዘጋጀት

15.1 የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወይም ቅርንጫፎችን /አክሲዮን ማህበራትን ዓመታዊ የሽያጭ ፍላጎት በመለየት ለመንግስት የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል

15.2 የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች/አክሲዮን ማህበራት ለመሸጥ በመርሐ-ግብር የተደገፈ የሽያጭ ዕቅድ ማዘጋጀት አለበት።

15.3 የሽያጭ ዕቅዱ የሽያጩን ጊዜ፤ የሚሸጠውን ድርጅት፤ ቅርንጫፍ/አክሲዮን ማህበራት፤ የሽያጩ መጠንና ለሽያጩ ተስማሚ የሆነ የሽያጭ ስልት ዓይነት ማካተት ይኖርበታል።

16 የሽያጭ ዕቅድ የሚፀድቅበት እና የሚሻሻልበት ሁኔታ

16.1 የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተደደር ዘርፍ ያዘጋጀውን ዓመታዊ የሽያጭ ዕቅድ ለሚ/ር መ/ቤቱ አቅርቦ ያፀድቃል።

16.2 የኮርፖሬት ፋይናንስ አስተደደር ዘርፍ የሽያጭ አፈፃፀም ሂደት በፀደቀው የሽያጭ ዕቅድ መሠረት መመራቱን ማረጋገጥ አለበት።

14 ምልዓተ-ጉባዔና ውሣኔ

14.1 ኮሚቴው የግምገማ ሥራውን ለማከናወን ምልዓተ-ጉባዔ የሚኖረው ከአባላቱ ሁለት ሦስተኛው ሲገኙነው።

14.2 የኮሚቴው ውሣኔ የሚባለው ከተገኙት ሁለት ሦስተኛ አባላት የድምጽ ብልጫ ያገኘው ሃሣብ ነው። ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሣቢው ያለበት ወገን ድምጽ የኮሚቴው ውሣኔ ሆኖ ይቆጠራል።

ክፍል 3

ስለ ሽያጭ ዕቅድ

15 የሽያጭ ዕቅድ ስለማዘጋጀት

15.1 የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወይም ቅርንጫፎችን /አክሲዮን ማህበራትን ዓመታዊ የሽያጭ ፍላጎት በመለየት ለመንግስት የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል

15.2 የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች/አክሲዮን ማህበራት ለመሸጥ በመርሐ-ግብር የተደገፈ የሽያጭ ዕቅድ ማዘጋጀት አለበት።

15.3 የሽያጭ ዕቅዱ የሽያጩን ጊዜ፣ የሚሸጠውን ድርጅት፣ ቅርንጫፍ/አክሲዮን ማህበራት፣ የሽያጩ መጠንና ለሽያጩ ተስማሚ የሆነ የሽያጭ ስልት ዓይነት ማካተት ይኖርበታል።

16 የሽያጭ ዕቅድ የሚፀድቅበት እና የሚሻሻልበት ሁኔታ

16.1 የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ ያዘጋጀውን ዓመታዊ የሽያጭ ዕቅድ ለሚ/ር መ/ቤቱ አቅርቦ ያፀድቃል።

16.2 የኮርፖሬት ፋይናንስ አስተዳደር ዘርፍ የሽያጭ አፈፃፀም ሂደት በፀደቀው የሽያጭ ዕቅድ መሠረት መመራቱን ማረጋገጥ አለበት።

ክፍል 4

የሽያጭ አፈጻጸም

17 የተፈቀደ የሽያጭ ዘዴ

በዚህ መመሪያ መሰረት የሚካሄደው የሽያጭ አፈፃፀም ዘዴ ግልፅ ጨረታ ነው

18 ግልጽ ጨረታ

18.1 ግልጽ ጨረታ ሽያጩ ስራ ሽፋን እንዲያገኝ በሬዲዮ፣ በጋዜጣና በሌሎች ልዩ ልዩ የብዙሐን መገናኛ ዘዴዎች ተጫራቾችን በመጋበዝ ተግባራዊ የሚሆን የሽያጭ ስልት ሲሆን በግልጽ ጨረታ የሚሸጡ የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበሮች ለብዙ የአገር ውስጥ እና ለውጭ ባለሀብቶች እንዲታወቁ ያደርጋል።

18.2 ግልጽ ጨረታ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

ሀ/ የጨረታ ማስታወቂያ አግባብነት ባለውና ሰፊ ሽፋን ባለው ሚዲያ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ ገጽ ቢያንስ አንድ ጊዜ እንዲወጣ ይደረጋል።

ለ/ ተጫራቾች በቂ የጨረታ ማዘጋጃ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማስቻል በዚህ መመሪያ ላይ በግልጽ በተጠቀሰው መሰረት ከ60 ቀናት ያላነሰ ጊዜ ይሰጣቸዋል።

ሐ/ የውጭ አገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋና የጨረታ ዋስትና በአሜሪካን ዶላር ወይም በዩሮ መቅረብ ይኖርበታል።

ክፍል 5

የጨረታው ሂደትና ውሳኔ አሰጣጥ

19 የሽያጭ ጨረታ ሰነድ ዝግጅት

19.1 የጨረታ ሰነድ የሚዘጋጀው የፀደቀው የዋጋ ትመና በተዘጋጀበት የኢንቨስትመንት አስተዳደርና እና ፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት ይሆናል፤

19.2 በተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ የህግ ዳይሬክቶሬት አስተያየት መስጠት አለበት። የኢንቨስትመንት አስተዳደርና እና ፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት አስተያቱን የማይቀበልበት በቂ ምክንያት ካለው ከህግ ዳይሬክቶሬት ጋር በመወያየት ማስተካከል ካልተቻለ የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

19.3 ለሽያጭ የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ኮፒ የሚ/ር መ/ቤቱን ኦርጅናል ማህተም የያዘ መሆን አለበት፤

19.4 በጨረታ ሠነድ የሚሠፍሩ መረጃዎች ከፀደቀው የዋጋ ትመና ሠነድ የተወሰዱና እንዳ አግባቡ ወቅታዊ የተደረጉ መሆን አለባቸው፤

19.5 በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚዘጋጅ የጨረታ ሰነድ ተጫራቾች የሚያቀርቡትን የጨረታ ሰነድ ማዘጋጅትና ማቅረብ እንዲችሉ ግልጽ ሆኖ፤ በቂና የተሟላ መረጃ መያዝ ይኖርበታል፣

20 የጨረታ ሰነድ ይዘት

የጨረታ ሰነድ እንደሚሸጠው ድርጅት ባህሪ በውስጡ ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

20.1 ለሽያጭ የሚቀርቡ ድርጅቶችን/ቅርንጫፎችን አፈፃፀምና ሁኔታ በሚመለከት፤

20.2 ለሽያጭ የቀረበውን ድርጅት ስም፣ አድራሻና የተሰማራበትን የንግድ ሥራ መስክ፣

20.3 የድርጅቱን የማምረት/አገልግሎት የመስጠት አቅም፣ የምርት፣ የሽያጭ፣ የገበያ፣ የጥሬ ዕቃ፣ የፋይናንስ፡ የትርፋማነት አፈፃፃም፣ ወዘተ መረጃ ላለፉት ሦስት ዓመታት፣ ድርጅቱ ያለውን የሰው ኃይል በዕድሜ፣ በፆታ፣ የቅጥር ዓይነት (ቋሚ፣ ጊዜያዊ፣ ኮንትራት)፣ በትምህርት አጠቃሎ የሚያሣይ መረጃ (የመጨረሻ በጀት ዓመት)

20.4 የሚሸጠው ድርጅት የሚተላለፈው ከነ ቅርንጫፉ ከሆነ የቅርንጫፉን አድራሻ፣ ምርት ወይም አገልግሎት፣ ወዘተ የሚያሣይ መረጃ፣ በኦዲተር የተመረመሩ የሂሣብ መግለጫዎች ለሽያጭ የተጠቀመውን ያለፉት 3 ዓመታት፣ የቋሚ ንብረቶች ዝርዝር በመጠን፣ በዓይነትና በዕድሜ፣ በሽያጩ የማይካተቱ የድርጅቱ ይዞታዎች/ቅርንጫፎች ግንባታዎች ወዘተ፤

20.5 የማምረቻ መሣሪያዎች፣ የወርክ ሾፕ መሣሪያዎች፣ ቋሚ ተክሎች የቢሮ ቋሚ ዕቃዎች፤ ተሽከርካሪዎች ህንፃዎች፤

20.6 መሠረተ ልማቶች (የእርሻ መሬት፣ መንገድ፣ የቴሌፎን እና የመብራት አገልግሎቶች መስመሮች፣ የመስኖ መሠረተ ልማቶች፣ ወዘተ)፤

20.7 ከተጫራቾች ጋር የሚፈፀም ውል ናሙና፤

20.8 የማወዳደሪያ መስፈርቶች፤ክብደታቸው እና የምዘና ሁኔታ

ክፍል 6

የጨረታ አቀራረብ፣ መዝጊያ ጊዜ፣ አከፋፈትና አመዘጋገብና ሪፖርት

22 የጨረታ አቀራረብ (የጨረታ ሰነድ አሰባሰብ/መረከብ)

በጨረታ ሰነድ ርክክብ ሂደት ውስጥ መከናወን ያለባቸው ተግባራት እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡-

22.1 የተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን የጨረታ ጥሪው ላይ በተገለጸው ቦታ ጥሪ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ እስከመጨረሻው የመዝጊያ ሰዓት ድረስ ክፍት ሆኖ መገኘት ይኖርበታል፡

22.2 የጨረታ ሰነድ የሚቀርበው ለዚሁ በተዘጋጀውና በኮሚቴ አባላት ባዶ መሆኑ ተረጋግጦ በታሸገ ሣጥን ውስጥ በመክተት ነው።

22.3 የጨረታ ሳጥኑ ደህንነት የተጠበቀ መሆን ተገቢ ሲሆን ጨረታው እስከሚከፈት ድረስ ቁልፉ በሽያጭ/ ገምጋሚ ኮሚቴ ጸሀፊ እጅ ተይዞ መቆየት ይኖርበታል፡

22.4 የተጫራቾች ሰነድ በተዘጋጀው ሳጥን ገቢ መደረግ አለበት ፣ ሆኖም ግን የቀረበው የተጫራቾች ሰነድ በሳጥን ውስጥ ሊገባ የማይችል ጥቅል የሆነ እንደሆነ ሰነዱ ለኮሚቴው ፀሐፊ በእጁ ይሰጣል። ፀሐፊውም መረከቡን የሚያረጋግጥ መተማመኛ ለተጫራቹ መስጠት ይኖርበታል። በተጨማሪም ሁኔታው በፀሐፊው ተመዝግቦ ሰነዱ በጥንቃቄና በምስጢር ይያዛል። ስለዚሁ ሁኔታ በጨረታው መክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ ለሚገኙ ሁሉ ይገለጻል። የጨረታ ሰነዱም ከሌሎች የጨረታ ሰነዶች ጋር አብሮ እንዲከፈት ይደረጋል።

22.5 ከጨረታ ሰነድ ማስረከቢያው የመጨረሻ ቀንና ሰዓት በኋላ ዘግይቶ የደረሰ የመጫረቻ ሰነድ ተቀባይነት የለውም።

23 የጨረታ መዝጊያ ጊዜ

23.1 የጨረታ መዝጊያ ቀን፣ ቦታና ሰዓት በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ተገኝቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተራቅዶ የጨረታ ሰነዱን የገዙ ሁሉ በጽሁፍ እንዲያውቁት ካልተደረገ በስተቀር ተወዳዳሪዎችን ለመጋበዝ በወጣው ማስታወቂያ ላይ የተመለከተውን የጨረታ መዝጊያ ቀን፣ ቦታና ሰዓት መለወጥ አይቻልም።

23.2 የጨረታ መዝጊያው ቀን፣ቦታና ሰዓት ሲያበቃ ወዲያውኑ ሰብሳቢና ፀሐፊው፣ ጨምሮ አብላጫው የኮሚቴው አባላት ከጨረታ ማስገቢያው ሥፍራ ድረስ በመገኘት የጨረታ መቀበያውን ሣጥን ያሽጋሉ:: ማሸጊያው የእያንዳንዱን የተገኘውን የኮሚቴ አባል ፊርማ መያዝ አለበት:: ለመገኘት ያልቻለ የኮሚቴው አባል ያልተገኘበትን ምክንያት በጽሑፍ ለኮሚቴው ሰብሳቢ ማቅረብ አለበት::

24 የጨረታ መክፈቻ ጊዜ

ጨረታ የሚከፈተው ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ በወጣው ማስታወቂያ ላይ በተመለከተው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ ነው:: ለውጥ ለማድረግ የሚቻለው በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ሲገኝ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒስትር ፈቃድ ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ የወጣው የጨረታ ሰነድ የገዙት ሁሉ በቅድሚያ በጹሁፍ እንዲያውቁት ከተደረገና ቢያንስ የአንድ ሣምንት ጊዜ ከተሰጠ በኋላ ነው::

25 የጨረታ አከፋፈት ሥርዓት

25.1 ጨረታው የሚከፈተው በጨረታው ጥሪ ወይም ማሻሻያ ተደርጎ ከሆነ በማሻሻያ ሰነዱ ላይ በተገለጸው ቀን፣ሰዓትና ቦታ በግልጽ ይሆናል፤

25.2 ጨረታው የሚከፈተው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው እንዲሁም ቢያንስ ሃምሳ ከመቶ የኮሚቴው አባላት በተገኙበት ነው:: ሆኖም ተጫራቹ በራሱ ምርጫ የጨረታውን መከፈት ሳይገኝ መቅረቱ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ አያስተጓጉለውም፤

25.3 የጨረታውን አከፋፈት ሂደት እስካላወከና በቂ ቦታ እስካለ ድረስ በጨረታው መክፈቻ ሥነ- ሥርዓት ላይ ማንኛውም ታዛቢ መገኘት ይችላል፤

25.4 የጨረታው ሳጥን ሲከፈት የተገኙ ፖስታዎች ይቆጠራሉ፣ ሣጥኑ በአግባቡ የታሸገ፤ ፖስታዎቹ እሽጋቸው ያልተነካ/ያልተከፈተ መሆኑ ይረጋገጣል፣

25.5 ፖስታዎች በሙሉ ተከፍተው በውስጣቸው ያለው ወረቀት ገጽ ብዛት ተቆጥሮ ቁጥር ይጻፍበታል፤

25.6 የሽያጭ ኮሚቴ አባላት በእያንዳንዱ ሰነድ ገጽ ላይ ይፈርማሉ፤

25.7 የጨረታ ሰነድ ሲከፈት የጨረታ ማስከበሪያ በ[illegible] ማስያዛቸው ይረጋገጣል፤

25.8 የጨረታ ማስከበሪያ ያላስያዘ ተጫራች ከ[illegible] ጨረታው ውጭ እንዲሆን ይደረጋል፤

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Public Enterprises

25.9 የጨረታው ሂደት በቃለ ጉባኤ ይያያዛል በጨረታው ላይ የተገኙት የኮሚቴ

25.10 አባላት የሥራ ኃላፊዎች በቀረበው ሰነድ ላይ ይፈርሙበታል፣

25.11 የጨረታው ውጤት ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ የጨረታው ዝርዝር ትንተና

25.12 በሚስጥር መጠበቅ ይኖርበታል፤

25.13 ማንኛውም በጨረታ መክፈቻ ሥርዓት ላይ ያልተከፈተና ለተጫራቾች ያልተነበበ

25.14 የመጫረቻ ሰነድ ለቀጣይ ውድድር ሊያገለግል አይችልም፤

25.15 በመክፈቻው ላይ የተገኙት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በመክፈቻው ላይ ለመገኘታቸው ማረጋገጫ እንዲፈርሙ ተደርጎ ፊርማው የጠቅላላው የጨረታው ሂደት ሰነዶች አካል ይደረጋል፤

25.16 ሣጥኑ ከተከፈተ በኋላ እያንዳንዱ ተጫራች ያቀረበው ሰነድ እየታየ ለጨረታው ምላሽ የሰጠው የጨረታ ሰነዱን የገዛው ሰው ስለመሆኑ ከዋናው መዝገብ ጋር በማመሳከር በቅድሚያ ይረጋገጣል። የጨረታ ሰነዱን ያልገዛ ሰው ያቀረበው የጨረታ ሰነድ ዋጋ የለውም፤

25.17 የጨረታ ኤንቨሎፕ ከሣጥኑ ሲወጣ ክፍት ሆኖ ከተገኘ ወይም በፀሐፊው እጅ የነበረ የጨረታ ሰነድ እሽግ ክፍት ሆኖ ከተገኘ የተገኘበት ሁኔታ በግልጽ በቃለጉባዔ ተመዝግቦ ይያዛል። የዚህ ዓይነት የጨረታ ሰነድ ዋጋ ያለው መሆን ስለመሆኑን ኮሚቴሚው በሚያቀርበው የውሳኔ ሃሳብ መነሻነት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒስትር ውሳኔ ይሰጥበታል፤

25.18 የጨረታ ሰነዱን የገዙና ለእያንዳንዱ የልማት ድርጅት፣ቅርንጫፍ / አክሲዮን ማህበር የቀረቡት ተጫራቾች /ክፍት ሆኖ የተገኘን የጨረታ ምላሽ ጨምሮ/ ስምዝርዝር፣ እያንዳንዱ የተጫረቱበት ድርሻ መጠን ያቀረበው ዋጋ ዝርዝር ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናና መጠኑ፣ የቀረበ ቢዝነስ ፕላን እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ነው ተብሎ የታመነበት ዝርዝር በኮሚቴው ሰብሣቢ ወይም በፀሐፊው አማካኝነት በንባብ ለተሣታፊዎች ይገለጻል።

25.19 ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ከተፈጸመ በኋላ ጠቅላላውን የጨረታውን ሂደትና ክንውን የሚገልጽ ቃለጉባዔ በመክፈቻው ላይ በተገኙት የኮሚቴው አባላት ተፈርሞ በሰብሣቢው አማካኝነት ከሦስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒስትር ይቀርባል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia ... Enterprises

26 ሪፖርት

ኮሚቴው ወደ ዝርዝር ግምገማው ከመግባቱ በፊት ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 24 ከተመለከተው በተጨማሪ የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች የያዘና ሁሉንም ተጫራቾች የሚያጠቃልል በሠንጠረዥ የተዘጋጀ ሪፖርት በሰብሣቢው አማካኝነት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒስትር ይቀርባል። ዝርዝር ነጥቦችም፡-

ሀ/ የተወዳዳሪውን ሙሉ ስም

ለ/ ጉዳዩ የሚመለከተውን የልማት ድርጅት ስም

ሐ/ ተጫራቹ የሚጫረትበትን ድርሻ መጠን

መ/ ተጫራቹ የሰጠውን ዋጋ

ሠ/ ተጫራቹ የሰጠው የቢዝነስ ፕላን በአጭሩ ✓

ረ/ ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ በወጣው ማስታወቂያ ላይ የተመለከቱት ግዴታዎች መሟላት አለመሟላታቸውንና የታየውን ልዩነት በአጭሩ

ሰ/ ሌላ ለማንዛቤ አስፈላጊ ነው ተብሎ የሚገመት መረጃ ናቸው።

27 የሽያጭ ጨረታ መወዳደሪያ መስፈርቶች

ለማንኛውም ሽያጭ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት መስፈርቶችን ወይም መመዘኛዎችን ያሟላ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል። ዋና ዋናዎቹ የሽያጭ መመዘኛዎች የሚከተሉት ናቸው።

28 የጨረታ ዋጋ /ፋይናንሽያል ፕሮፖዛል/

በማንኛውም ሽያጭ ላይ ተወዳድሮ ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበ ና የቢዝነስ ፕላን መመዘኛዎችን ያሟላ ተጫራች የውድድሩ ወይም የጨረታው አሸናፊ ይሆናል

28.1 በተጫራቾች በሚቀርበው የጨረታ ዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ላይ፡-

ሀ/ የተጫራቹ ሙሉ ስም፣ ዜግነትና አድራሻ

ለ/ ተጫራቹ የተጫረተበት ድርጅት/አክሲዮን ማህበር ስም

ሐ/ ተጫራቹ የድርጅቱን/የአክሲዮን ማህበሩን ምን ያህል ድርሻ (%) ሊገዛ እንደፈለገ፣

መ/ ድርጅቱን ወይም እያንዳንዱን አክስዮን ማህበር የሚገዛበት ዋጋ መጠን በአሃዝና በፊደል

The Federal Democratic Republic of Ethiopia ... Enterprises

ሀ/ የመሸጫ ዋጋ የመክፈያ ሁኔታና ጊዜ (Term of Payment) በግልጽ ሰፍሮ ወይም ተጽፎ መቅረብ አለበት።

28.2 ቴክኒካል ፕሮፖዛል /ቢዝነስፕላን

በዋጋና በቢዝነስ ፕላን አወዳድሮ የልማት ድርጅቶችን /አክሲዮን ማህበራት ሽያጭ ማከናወን ሲፈለግ የቢዝነስ ፕላንና ዋጋ የያዘ የጨረታ ዶክመንት አዘጋጅተው የሚያወዳድሩበት የሽያጭ ስልት በመጠቀም መ/ቤቱ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ በዋጋና በቢዝነስ ፕላን ለየብቻ ማወዳደርና ሽያጭ ማከናወን ይችላል።

28.3በተጫራቾች የቀረቡት ፕሮፖዛሎች የሚገመገሙባቸውና የሚበላለጡባቸው መስፈርቶች ከአንዱ ድርጅት ወደ ሌላው ሊለያዩ የሚችሉ ቢሆኑም በኢኮኖሚውና በመሠረተልማት ውስጥ ያላቸው አስተዋጽኦ፣በወጪ ንግድ ከሚኖራቸው ሚና፣ከትርፋ ማነት ወዘተ አንጻር እየታየ ክብደት የሚሰጣቸው ሲሆን ዋና ዋና መስፈርቶቹ ግን የሚከተሉት ይሆናሉ።

ሀ/ ግልጽ እና እርስ በርስ የተጣጣመ፣ ✓

ለ/ የሚሆሩ የማስፋፋት፣ የማደስ፤ የማሻሻልና የግንባታ ሥራዎች ቅደም ተከተልና ይህም የሚወስደውን ጊዜና የገንዘብ መጠን ያመላከተ፣ ✓

ሐ/ የገዥ ድርጅትን የፋይናንስ አቅም የሚያሣይ፤ ኦዲት የተደረጉ የሂሣብ መግለጫዎችን ወይም የባንክ ማስረጃዎችን ያካተተ፣ ✓

መ/ ለወደፊቱ የሚደርስባቸውን ግቦች የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል፤ ✓

ሠ/ ሥራን የመፍጠርና፣ሠራተኞን የማሰልጠን እቅድ፤ ✓

ረ/ የውጭ ምንዛሪን የማስገኘት እቅድ፤ ✓

ሰ/ ዘመናዊ አሠራርን የማስረጽ እቅድ፤ ....ወዘተ

28.4 የጨረታ መክፈቻ ጊዜ ስለማራዘም

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጨረታ መዝጊያ ጊዜን ከተወሰነው ጊዜ በላይ ማራዘም ይቻላል።የጨረታ መዝጊያ ጊዜን ማራዘም የሚቻለው ከሚከተሉት አንዱ ሁኔታ ሲከሰት ነው፡-

ሀ. የጨረታ ሰነድ የገዙ ተጫራቾች ጊዜ እንዲራዘምላቸው ከጨረታው መዝጊያ ጊዜ ከ10 ቀናት በፊት ሲጠይቁ፤

ለ. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት ጊዜውን ማራዘሙ ጠቃሚ ሆኖ ሲያገኘው ጨረታው በወጣበት መገናኛ ብዙሀን ማስታወቂያ ያወጣ እንደሆነ፤

ሐ. ግዜውን ማራዘም የሚቻለው በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ሲገኝ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒስትር ፈቃድ ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ የወጣው የጨረታ ሰነድ የገዙት ሁሉ በቅድሚያ በጹሁፍ እንዲያውቁት ከተደረገና ቢያንስ የአንድ ሣምንት ጊዜ ከተሰጠ በኋላ ነው።

29 ጨረታን ስለመሠረዝና ተጫራቾችን ከውድድር ስለማስወጣት

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ ከተሟላ ያወጣውን የሽያጭ ጨረታ መሠረዝ ይችላል፤

29.1 ለጨረታው የቀረቡት ተወዳዳሪዎች ያቀረቡት ሰነድ ድርጅቱ ካዘጋጀው ዝርዝር የጨረታ መመሪያ/መስፈርት ጋር ፈጽሞ የማይጣጣም ሆኖ ሲገኝ፣

29.2 ተጫራቾች የጨረታ ህግና ደንብን ያልተከተሉ ከሆነ ወይም ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት የተፈጠረ መሆኑ ሲረጋገጥ

29.3 የቀረበው የጨረታ ዋጋ ከቀረበው የመሸጫ ጠቋሚ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ያነሰ ሆኖ ከተገኘና ከአሸናፊዎች ጋር መደራደርና መስማማት ካልተቻለ፣ ጨረታው ይሰረዛል፤

29.4 ፕሮፖዛሉችና ዋጋዎች ይህንን መመሪያ ወይም ተወዳዳሪዎችን ለመጋበዝ በወጣው ማስታወቂያ ላይ የተመለከቱትን የመወዳደሪያ መስፈርቶች ያልተከተሉ መሆናቸውን ሲያምን፤

29.5 ተጫራቹ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ወይም የውል ማስከበሪያ ያላስያዘ እንደሆነ፣

29.6 ስርዝድልዝ ያሰበት ወይም የማይነበብ መወዳደሪያ ወይም ፕሮፖዛል ማቅረብ፡

29.7 መወዳደሪያ ዋጋ ያልያዘ ሰነድ ማቅረብ፤

29.8 ለማናቸውም የሚኒስቴሩ ሠራተኛጉቦ ወይም መደለያ መስጠት ወይም የተሰየ ጥቅም ለማግኘት መሞከር፤

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of P... Enterprises

ክፍል 7

የጨረታ ሠነድ ግምገማና ማወዳደር

30 የጨረታ ሠነድ ግምገማ

ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን /አክሲዮን ማህበራትን ለመግዛት ተጫርቶ በቅድሚያ በጨረታ ሰነዱ ውስጥ በተጠቀሱት የመመዘኛ መሥፈርቶችና ዝርዝር መግለጫ መሠረት ተገምግሞ የሚከተሉትን አሟልቶ የተገኘ ተጫራች በውድድሩ አሸናፊ ይሆናል፣አመራረጡ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

29.1.በቢዝነስ ፕላንና የፋይናንስ አጠቃላይ ግምገማ ድምር ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘውን ተጫራች ይመርጣል፤

29.2 በግምገማ ወቅት ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ተጫራቾች እኩል ነጥብ ቢያገኙ ለሴት ተወዳዳሪዎች ቅድሚያ ይሰጣል።

29.3 ከላይበተራ ቁጥር 31.2 የተጠቀሰው እንተደጠበቀ ሆኖ ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ተጫራቾች እኩል ነጥብ ቢያገኙ አሸናፊውን ለመለየት እኩል የወጡ ተጫራቾች በተወሰኑ መሥፈርቶች ላይ የመጨረሻ የመወዳደሪያሐሳባቸውን እንዲሰጡ ማድረግ ይቻላል፤

29.4 ተጫራቾች ለሁለተኛ ጊዜ በተወዳደሩበት መስፈርት እኩል ከወጡ ተጫራቾች በተገኙበት በዕጣ ይለያሉ።

31 ጨረታን ማጽደቅና የጨረታ አሸናፊውን ማሳወቅ

31.1 ኮሚቴው ተግባሩን አጠናቆ እያንዳንዱን ተጫራች በተመለከተ ትንተናና የደረሰበትን መደምደሚያ፣የአሸናፊዎችን ቅደም ተከተል፣ከዚህ ቅደም ተከተል ላይ ለመድረስ ያበቁትን ምክንያቶችና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ መገለጫዎችንና የኮሚቴውን የውሣኔ ሃሣብ የያዘ ዝርዝር የጽሑፍ ሪፖርት ያዘጋጃል። አነስተኛው ድምጽ እንዲሁም ሌሎች በልዩነት የተሰጡ ውሣኔዎች /አስተያየቶች/ ከምክንያቶቻቸው ጋር በሪፖርቱ ውስጥ መካተት አለባቸው።

31.2 የመንግስት የልማት ድርጅቶችን/አክሲዮን ማህበራትን ሽያጭ አስመልክቶ የጨረታው ግምገማ እንደተጠናቀቀ የውሳኔ ሃሳብ በኮሚቴው ሰብሣቢ በተፈረመ ሸኚ ደብዳቤ [illegible] መ/ቤቱ ሚኒስትር ይቀርባል ፤

31.3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አሸናፊ ለሆነው ተጫራች በ10 ቀን ውስጥ ክፍያ ፈጽሞ ውል እንዲፈርም በጽሑፍ ያሳውቃል፤

31.4. የጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ ሁለተኛ የወጣውን ተጫራች አሸናፊ ማድረግ ወይም አዲስ ጨረታ ማውጣት ይችላል፣

31.5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአሸናፊው ተጫራች ክፍያ ከፈጸመና ውል ከተፈረመ በኋላ የተሸናፊ ተጫራቾችን የጨረታ ማስከበሪያ መመለስ ይኖርበታል፤

31.6. የጨረታ አሸናፊው በውሉ መሠረት አለመፈፀሙ ሲረጋገጥ ለዋስትና ያስያዘው ሙሉ በሙሉ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ገቢ መሆን አለበት ፤ውሉ ያልተፈጸመው በተጫራቹ ሳይሆን በራሱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ መሆኑ ከተረጋገጠ የውል ማስፈጸሚያ የተያዘው ለተጫራቹ ሊመለስለት ይችላል።

32 ውል መፈረም

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውም የመደበኛ ጨረታ ሰነድ አንድ ክፍል የሆነውን የውል ናሙና መሰረት በማድረግ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሰነድ በማዘጋጀት ከሽያጭ ጨረታ አሸናፊው ጋር መፈራረም አለበት። ውሉ ሲፈረም የሚከተሉት የውል ሁኔታዎች መካተት ይኖርባቸዋል፡-

32.1 በውሉ መሠረት የሚሸጠው የልማት ድርጅት /አክሲዮን ማህበር ርክክብ የሚፈጸምበት አኳኋን ወይም የማስረከቢያ ቦታና ጊዜውን፣ የሚከፈለውን አጠቃላይ ዋጋ መጠን የአከፋፈል ሁኔታ እና የክፍያ ጊዜውን፤

32.2 በውል አፈጻጸም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበትን አካሄድ ማመላከት፣

32.3 የውጭ አገር ተጫራቾች ጠቅላላ የውሉ መጠን በውጭ አገር ገንዘብና በብር ሲከፈል የሚገባውን የገንዘብ መጠን፣

32.4 ገዢው በውሉ በተመለከተው መሰረት ካልፈጸመ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚወስደውን እርምጃ፤

32.5 ከትመና በፊትም የነበረ የአ/አክሲዮን ማህበሩ ንብረት ሆኖ ከትመና በኋላ በአክሲዮን ማህበሩ የተገዛ ወይም የተገነባ የአክስዮን ማህበሩንብረት እንዲሁም የአክስዮን ማህበሩ ባልሆነ ገንዘብ የተገዛ ወይም በስጦታ የተገኘ የመንግስት ንብረት ካለ ከሽያጩ ዋጋ በተጨማሪ ገዥ በሚተምነው መሰረት እንደሚከፍል፤

[illegible] ድርጅቶችን ወደግል እንዲዛወር ለማድረግ የልማት ድርጅቶችን ዋጋ ለመወሰን[illegible] በተካሄደው ትመና ያልተካተተ ሆኖ በርክክብ ወቅት በመብሰጥ

የሚገኘው ንብረት ከትመናው ጊዜ በፊት የነበረ ንብረት ወይም ከትመናው ቀን በኋላ የተገዛ ንብረት ወይም የተገነባ ህንፃ ካለ ከሽያጩ ዋጋ በተጨማሪ ገገር በሚተመነው መሰረት እንደሚከፍል፤

32.7 ከእዳ ነፃ ማስረጃ ለገገርዎች ከተሰጠም በኋላ ቢሆን በሂሳብ ስሌት ስህተት ምክንያትያልተከፈለቀሪገንዘብመኖሩንሚ/መ/ቤቱ ካረጋገጠና ሂሳቡንም በተጨባጭ ማስረጃ አስደግፎ ካቀረበ ክፍያውን የመጠየቅ መብት እንደሚኖረው፤

32.8 በተሸጠ ድርጅት ስም ለመብራት፣ ለውኃና መገናኛ ብዙሃን ለአገልግሎት ሰጪ መ/ቤቶች ለኢንሹራንስ ዋስትና በቅድሚያ ወይም በመያዣነት የተከፈለ ማናቸውም ገንዘብ ካለ ጥቅም ላይ ያልዋለውን መጠን ያህል ታስቦ ገዥው ለሻጭ እንደሚከፍል፤

32.9 እስከ ርክክብ ቀን ድረስ ያሉትንና ለሻጭ መከፈል ያለባቸውን የትርፍ ድርሻ ክፍያዎች በኦዲት ሪፖርት ወይም በጊዜያዊ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት መሰረት ሙሉ በሙሉ በውሉ በሚመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አጠናቆ ክፍያውን መፈጸም እንደሚኖርበት፤

32.10 ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ለአክሲዮን ማህበሩ ቀደም ሲል የተሰጠ ብድር ካለ በውለታው መሰረት በውሉ በሚመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገዥ አጠናቆ ክፍያውን እንዲፈጽም፤

32.11 ገዥ ያቀረበው የወደፊት የሥራ ዕቅድ የውሉ አካል ሆኖ የተያያዘውን ዕቅድ /ቢዝነስ ፕላን/ በሽያጭ ውሉ በተመለከው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት እና ተግባራዊ ባያደርግ የሚወሰደውን እርምጃ፤

32.12 የሽያጭ ውሉ አንዱ አካል ሆኖ በቀረበው ዕቅድ /ቢዝነስ ፕላን/ ላይ የተመለከቱት የማስፋፊያና የማሻሻያ ስራዎች በገዥ በትክክል መተግበራቸውን ሻጭ ክትትል እንደሚያደርግ ውሉ ሲፈረም መካተት ይኖርበታል።

33 የውል አስተዳደርና ውልን ተፈጻሚ ስለማድረግ

33.1 ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር የተደረጉ የውል ስምምነቶች ተፈጻሚ መሆን አለባቸው፤

33.2 ገዥ በውሉ መሠረት የውል ግዴታውን ካልፈጸመ አለመፈጸሙን የኢንቨስትመንት አስተዳደርና ፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክትሬት በፍጥነት ለህግ ዳይሬክቶሬት ማሳወቅ አለበት፡፡ የህግ ዳይሬክቶሬትም ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

33.3 በውል አፈጻጸም ወቅት እንደሁኔታው የውል ማሻሻያ ማድረግ የሚቻል ሲሆን የሚደረገው የውል ማሻሻያ የሚኒስቴር መ/ቤቱን ጥቅም የሚጎዳ እና ለገዢው የተለየ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም፤

34 ውል ማጠናቀቅ

በመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴርና በግል ባለሀብቶች መካከል የተፈረሙ የሽያጭ ውሎች እና ተያያዥ ጉዳዮች መጠናቀቃቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉት መከናዎን ይኖርባቸዋል፡-

34.1 ገዥው በውል ስምምነቱ መሠረት መክፈል ያለበትን ክፍያ እና የቢዝነስ ፕላን መፈጸሙን፤

34.2 በውሉ መሠረት የተያዙ ዋስትናዎች (ጋራንቲዎች) ተገቢው ክትትል የተደረገባቸው እና አስፈላጊ በሆነ ወቅት ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን፤

34.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከገዢ ጋር ያሉ ሂሳቦችን በመዝጋት እንደአስፈላጊነቱ የአፈጻጸም ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ክፍል 8

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

5 የሽያጭ አፈጻጸም ሪፖርት ስለማቅረብ

የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ የሽያጭ አፈጻጸም ዝርዝር ሪፖርት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒስትር ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

6 የቅሬታ አቀራረብ

34.1 በኮሚቴው ግምገማ ውጤት ቅር የተሰኘ ተጫራች የግምገማው ውጤት እንደገና እንዲታይለት የቅሬታ አቤቱታውን ለሚኒስትር አቅርቦ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

34.2 የጨረታው ገምጋሚ ኮሚቴ የጨረታውን ወይም የአቤቱታውን ውጤት ለተጫራቾች ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ ተጫራቾች አቤቱታ/ቅሬታ ካላቸው ማቅረብ እንዲችሉ 7/ሰባት/ የሥራ ቀናት ሊጠብቃቸው ይገባል፡፡

34.3 አቤቱታው በስምምነት ካልተፈታ በስተቀር አቤቱታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 10 የሥራ ቀናት ውስጥ ለቀረበው አቤቱታ ውሳኔውን በጽሑፍ መስጠት ይኖርበታል::

34.4 የተሰጠው ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ5 ቀናት ውስጥ ለአቤቱታ አቅራቢው መድረስ ይኖርበታል::

34.5 አቤቱታ የቀረበበት ማናቸውም ሽያጭ የሚጣራው ለጨረታው የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ፣ ሽያጭን በተመለከተ የወጣ የመንግስት አዋጅ፣ሌሎች ከሽያጭ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ህጎችና ይህን መመሪያ መሠረት በማድረግ ብቻ ይሆናል::

34.6 ለሚኒስትር የቀረበው አቤቱታ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ጨረታው ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ ይቻላል ::

37 ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸዉ ጉዳዮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያእና የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም::

38 መመሪያውን ስለማሻሻል

ማናቸውም በዚህ መመሪያ ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ለማናጅመቱ ቀርቦ ፀድቆ በሥራ ላይ እንዲውል ካልተፈቀደ በስተቀር ተፈጻሚነት የለውም::

39 መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከግንቦት 30 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ፀድቋል::

አዲስ አበባ ሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም.

ደሚቱ ሀምቢሣ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር